# ጅል አይሙት እንድያጫውት ይባላል።

ለዘብተኛ እየተባለ ለአመታት ሲሞገስ የኖረው እስስቱ መራራ ጉድና የመጨረሻው ሰአቱ ማንነቱንና ድብቅ ፍላጐቱን ፍንትው አድርጐን እያሳዬን ነው።ይህ ድብቅ ፍላጐቱ ደግሞ ገና መንግስት ሳይሆን ከአሁኑ በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት ሀይማኖትን የፖለቲካ ማሯሯጫ አድርጐ በማያያዝ ፣ፀረ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ዘመቻና ቅስቀሳ እያካሄዱ ነው።

ይህንን የዜማ፣ የቅኔና የፊደል ምንጭ የሆነ ታሪካዊና ሀገራዊ ታቋም ሰሞኑን እሱ በሚመራው ፓርቲ የተሰባሰሰቡና በበታችነት ስሜት እየተሰቃዩ ማንነታቸው የተሰወረባቸው አካላቶች፣ይህንን ሀይማኖታዊ ትንኮሳና ጥላቻ ንግግር በአደባባይ በድፍረት ሲናገሩ በሀላፊነት እንደማይጠየቁ ጠንቅቀው ስለሚያውቁ ነው።

ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንንና ተከታዮቹን ማጥፋትና መበተን የአብይ አህመድም ተልዕኮና ፍላጐትም እንደሆነ ስለተረዱ በድፍረት ዘመቻ ከፍተዋል።የጥላቻ ንግግርን ለመቆጣጠር ህግ አወጣሁ ያለ፣ ሸምድምድ መንግስት፣ እንድህ አይነት አንዱን በአንዱ ላይ የሚያነሳሳ የአደባባይ ንግግር ሲነገር ፣ በአልሰማሁም ምች የተመታው አብይአህመድ፣ አሁንም አልሰማሁምእኮ እንደሚለን ሳይታለም የተፈታ ነው።

የሚያሳዝነው የታገቱ ተማሪዎችን ማስለቀቅ ያቃተውና ግን ባንድራ እያወረደ ለመጣል ጉልበት ያገኘው የክልሉ ፖሊስ አብሮ ቆሞ ለንግግሩ ሲያጨበጭብ መታዬቱ ፀረ ኦርቶዶክስ ዘመቻው መንግስታዊ ድጋፍና እገዛ እንዳለው ግልፅ ማሳያ ነው።ሌላው አሳዛኙና አሳፋሪው ደግሞ የሀይማኖቱ መሪዎች ህልውናቸው እየተዋረደና ጦርነት እየተከፈተባቸው እያዩ እየሰሙ ዝምታን መምረጣቸው ችግራችን ምን ያህል ጥልቅ እንደሆነ ያሳያል።

አብዱ አሊ

20/01/2020